መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን
አይገባውም። ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም
ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል። ማቴ 10:39_39




እግዚአብሔር አምላክ ነፍሳችሁን በቅዱሳን አባቶች ጎን ያሳርፍ

# የእምነት አርበኛ

ምን እንደበት ይፈታዋል
ምንስ እንጀት ይትለዋል
ምንስ ቋንቋ ይገልጸዋል
ሰው እንደ ጠቦት ሲታረድ
የፊጦን ታሥሮ በገመድ
አልወጣም ብሎ ከተዋሕዶ መንገድ
የአምላኩን ቃል ሊመሰክር
እምነቱ በእሳት እንደሚፈተን ሊያዘክር
ሰማያዊ አክሊልን ሊደፋ
የጽድቅ ሕይወቴ ሆኖት ተስፋ
ኢትዮጵያዊው የእምነት አርበኛ
ክርስቶስ አምላኩን አድርጐ ዳኛ
የቅዱስ ጊዮርጊስን ምግባር አንግቦ
የሰማዕቱ እስጢፋኖስ ውበት ተውቦ
የቅዱስ ጴጥሮስን ገድል አንብቦ
የእነ ጳውሎስን ጥንካሬ
የቅዱሳንን የሥራ ፍሬ
ትምክሕት ይሔነው ክብር
ማተቤ አይበጠስም ነገም ዛሬ
እያለ ሲሄድ በበረሃ
ምላስ ማርጠቢያ አጥቶ ውኃ
አጋጠመው የእምነት ድሀ
ካው መሳይ ጨካኝ አውሬ የማይሳሳ
በደም ሰክሮ የሚያገሳ
ኢትዮጵያዊው የድንግል ልጅ
እንዲህ አለ በተመስጦ
ወደ አምላኩ መሔዱን መርጦ
ኢትዮጵያዊው መልኩን
ነብር ዝንጉርጉርነቱን
መቼ ያውቃል ለውጦ?
እያለ ለራሱ ነግሮ
ይኸው ደረሰ በቀጠሮ
እምነቱን አስከብሮ
በአምላኩ እቅፍ ለማረፍ
ስሙ ከሰማዕታት ከቅዱሳን ጋር ሊጻፍ
አልፎ ሊገባ የገነትን ደጃፍ።

*ኃይለ መስቀል ተሰፋዬ ለንደን ሚያዚያ 2007*